# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 14 ኛ ሳምንት
## ድንግል ማርያም

**የትምህርቱ ዓላማ**

- ስለ ድንግል ማርያም ስንማር ለምን እንደምናከብራት እናያለን።

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***«ትውልድ ሁሉ ብፅእት ይሉኛል።»*** ሉቃ 1÷48

**ምንባባት**

- ሕዝቅ.44 እና ሉቃ 1

**መግቢያ**

- ድንግል ማርያም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ናት። የእግዚአብሔር እናትም ናት ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነውና። ጌታችን ከመወለዱ በፊት፣ ከወለደችውም በኋላ ድንግል ናት /ወትረ ድንግል/እግዚአብሔር ይሄን ምሥጢር ለነብዩ ሕዝቅኤል ገልጾለት ነበር። ***«ወደ ምሥራቁም ወደ ሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው የመቅደሱ በር አመጣኝ፣ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም፣ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።»*** ሕዝ. 44÷1-2

**ትምህርቱ**

- እመቤታችን ድንግል ማርያም ሃና እና ኢያቄም ከተባሉ ጻድቃን ባልና ሚስት በንጽሕና ተወልዳለች። ቤተሰቦቿ እግዚአብሔር ልጅ ተሰጣቸው የእግዚአብሔር አገልጋይ አድርገው እንደሚሠጥዋት ተስለው ነበር። ሦስት ዓመት ሲሞላትም እንደስለታቸው ወደቤተመቅደስ አስገቡዋት። ዳዊት ስለዚህ አስቀድሞ ተንብዮ ነበር።***«ልጄ ሆይ ስሚ፣ እይ፣ ጆሮሽንም አዘንብይ ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ፣ ንጉሥ ውበትሽን ወድዷልና»*** መዝ44/5/÷10
- ዳዊት ***«ልጄ»*** ያላት በእርሱ የዘር ሐረግ ስለምትወለድ ነበር። ***«ንጉሡ ውበትሽን ውድዷል።»*** ማለትም የሐሳብ የሥጋና ነፍስ ቅድስናሽን መርጦታል ማለት ነው። በቤተመቅደስ እግዚአብሔርን እያገለገለችና መልአኩ እየመገባት ኖራለች።
- 15 ዓመት ሲሞላትም እንዲጠብቃትና እንዲንከባከባት በመከራዋም አጋር እንዲሆናት በእድሜው ሽማግሌ ለነበረውና ለቅርብ ዘመድዋ ለዮሴፍ አደራ ተሰጠችው። በንጽሕናዋ እንደኖረችም የሕዝቅኤል ትንቢትና የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ***«ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ጌታ ከአንቺ ጋር ነውና፣ ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ»*** ሉቃ. 1÷28 የሚሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ያረጋግጣሉ።
- መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ዘካርያስን ካበሠረ ከ 6 ወር በኋላ ወደ እመቤታችን ተልኮ አበሠራት በድንግልና ጌታን እንደምትወልደውና ስሙንም ***«ኢየሱስ»*** ብላ እንደምትጠራው ነገራት። ይሄም የሚሆነው ምንም ነገር በማይሳነው በእግዚአብሔር መሆኑን ሲነግራት ***«እንደቃልህ ይሁንልኝ»*** አለችው።
- ከብሥራቱ በኋላም እመቤታችን ድንግል ማርያም ዘመድዋን ኤልሳቤጥን ልትጠይቅ ሄደች። ኤልሳቤጥ የመጥምቁ ዮሐንስ እናት ናት። ድንግል ማርያም ስትጎበኛትም የ6 ወር እርጉዝ ነበረች።
- እመቤታችንን ድምፅ ስትሠማም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት ፅንሱ/ዮሐንስ መጥምቅ/ በእናቱ ማህፀን ውስጥ በደስታ ዘለለ። ኤልሳቤጥም እንዲህ አለች ***«ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ፣ የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደእኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል።»*** ሉቃ .1÷41-42
- <u>ድንግል ማርያም ትሁት ነበረች</u>። እግዚአብሔር እናቱ ሆና ከእርስዋ ሊወለድ የመረጣትም በፍፁም ንፅሕንዋ ነበር። እርስዋም እግዚአብሔር ምክንያተ ድሂን/የመዳን ምክንያት/ አድርጐ እንደመረጣት ታውቅ ነበር። ትንቢቱም በእርስዋ ተፈፅሟል። እርስዋም ***«የባርያቱን ውርደት ተመልክቷልና። እነሆም ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና።»*** ሉቃ .1÷48-49
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው የመጀመሪያ ተዓምር ሆኖ በወንጌል የተመዘገበው ሲፈጸም በድንግል ማርያም አማላጅነት ነበር። ጌታችን ድንግል ማርያም እና አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በቃና ዘገሊላ ሠርግ ታደሙ። ሠርገኞቹ የወይን ጠጅ ሲያልቅባቸው ያየችው ድንግል ማርያም ወይን አልቆባቸዋል ብላ ለልጅዋ በመንገር ውሃ ተሞልቶ የወይን ጠጅ እንዲበረክትላቸው አድርጋለች። ዮሐ. 2÷1-11
- ጌታችን በመስቀል ሲሠቀል፤ ድንግል ማርያም ከወንጌላዊው ዮሐንስ ጋር ከመስቀሉ ሥር ነበረች። ጌታችንም እንዳታዝን አፅናንቶ ***«እነሆ ልጅሽ»*** ብሎአታል። ለዮሐንስም ***«እነሆ እናትህ»*** ዮሐንስም ወደ ቤቱ ይዞዋት ሄደ። እኛን ወክሎም ልጅ ሆናት።

**ማጠቃለያ፣**

- <u>ድንግል ማርያምን ማመስገን እንደሚገባ ከቅዱሳንና ከመላዕክት ተምረናል</u>። ከላይ እንዳየነው ሊቀመላዕክት ቅዱስ ገብርኤል እና ቅዱስ ኤልሳቤጥ አመስግነዋታል። እኛም ስናመሠግን ከቅዱሳንና ከመላእክት ጋር ህብረት እንፈጥራለን ማለት ነው። ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ነበር ያመሠገኑት። እኛም ስናመሠግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንፈፅማለን።
- <u>ድንግል ማርያም የእግዚአብሔር እናት ናት</u>፣ ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነውና። ለዚህም ነው ኤልሳቤጥ ***«የጌታዬ እናት»*** ያለቻት።

**ጥያቄ**

1. የድንግል ማርያም ዘለዓለማዊ ድንግልና የተጻፈው በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው? የመልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት የምናነበው በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው?ድንግል ማርያምን ማመስገን የተማርነው ከማን ነው? ድንግል ማርያምን የእግዚአብሔር እናት የምንላት ለምንድነው?
2. ጌታችን ያደገው የመጀመሪያ ተዓምር ሆኖ በንጌል የተጻፈልን ምንድነው? የት አደረገው?

**ተግባር**

- በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ /ሳምንት/ በድንግል ማርያም ሥዕሎች የምታዩትን በጽሑፍና በቃል አብራሩ።

**ይቆየን።**